

# አቲና ከኢየሩሳሌም ጋር ምን ንክኪ አላት?

ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ሳሰላስል ቆየሁኝ። የመጀመሪያ ጊዜዬ አልነበረም። የዛሬ 20 ዓመት ገደማ እንደዚሁ የመጀመሪያውን መጽሐፌን - ታቦት ከቤተ መቅደስ ወደ ቤተ ክርስቲያንን- እንዳሳትም አድርጎኛል። ከዚያም ምርምሬን በመቀጠል ጥያቄዎቼ አሳሳቢ የሆኑ ምላሾችን ሲያስገኙ ሁለተኛውን መጽሐፌን - የተሻለ እውነት በደብዳቤን - ለማሳተም በቅቻለሁ። አሁንም ባነበብኩኝ፣ በተመራመርኩኝ እና በጠያየኩኝ ቁጥር የማገኛቸው መልሶችና ግኝቶች እየረበሹኝና እያሳሳሰቡኝ መጥተዋል።

አንዳንድ የማገኛቸው እውነቶች በርግጥ በእውቅና እና በግልጽ ትምህርትና አቋም ስለማይሰጥባቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ኦፊሲያላዊ አቋም ለመሆናቸው ግልጽ የሆነ መረጃ የለም። ነገር ግን በተለያዩ የቤተ ክርስቲያኗ አገልጋዮች እና ተከታዮች በሚጻፉ ጽሑፎችና መጻሕፍት ላይ ስለሚገኙ የአብያተ ክርስቲያኗ አቋሞች ሆነው ለመወሰድ አያስቸግሩም። ከቅርብ ሳምንታት በፊት የተለያዩ የትምህርት ጽሑፎችን እያዘጋጀሁኝ በፌስ ቡክ ማስተላለፍ ጀምሬ ነበር። ሆኖም የሆነ መልዕክት ተለጥፎ አየሁና የተከታታይ ትምህርቱን መልዕክት አቋርጬ ይህንን መልዕክት ለመጻፍ ተገድጃለሁኝ። ተለጥፎ ያገኘሁት መልዕክት ስለ ኦርቶዶክስ ምሥጢራዊ (mystical) አስተምህሮ እና ልምምድ እንደዚሁም ስለ ኦርቶዶክስ ፍልስፍና ስለሚሰጥ የ online ትምህርት ማስታወቂያ ነበር። ማስታወቂያው በማብራራት፣ ትምህርቱን የሚከታተል ሰው ስለ "ጥንታዊቷ የኦርቶዶክስ እምነትና ትምህርት ግልጽ እና ተግባራዊ በሆነ መልኩ ስር የሰደደ እውቀት ለመገብየት እንደሚያስችል" ጨምሮ ገልጿል። እንደ ማስታወቂያው አገላለጽ ጥንታዊ የሆነው የኦርቶዶክስ ትምህርት በምሥጢራዊ (mystical) እና በፍልስፍና እውቀት ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ያሳያል። ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ ምሥጢራዊ (mystical) ትምህርት በክርስትና ብቻ የሚገኝ ትንክርት አይደለም። አይሁዶች ካባላ (kabbalah) የተሰኘ የእምነት ዘርፍና ትምህርት አላቸው። የእስልምና ሃይማኖት ደግሞ ሱፊዝም (Sufism) የሚባል ዘርፍ አላቸው። ከነዚህ የእምነት ዘርፎች ጋር በተመሳሰለ በክርስትና ውስጥ ያለው ዘርፍ ኦርቶዶክስ ነው ለማለት ባልደፍርም ተለጥፎ የነበረው የ online ትምህርት ማስታወቂያ ይህንን ለማለት የፈለገ ይመስላል።

ይህንን ጉዳይ ምንም ሳይገደኝ ዝም ብዬ ማለፍ እችል ነበር። ነገር ግን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን (ኢኦተቤክ) ጋር የተያያዘ መሆኑ ይህችን ጽሑፍ እንዳዘጋጅ ገፋፍቶ አስገድዶኛል። እንግዲህ ይህ - ማለትም ይህንን የ online ትምህርት ማስታወቂያ ያቀረበችው የኢኦተቤክ ባትሆንም - መረጃው ከአብያተ ክርስቲያኒቷ አጥባቂ ተከታይና ምዕመን የመጣ በመሆኑ በአንድም በሌላ መንገድ ትክክለኛ አቋም

ካልሆነ የኢኦተቤክ አቋሙን ማረም፣ ማስተባበል አሊያም መቃወም ይገባታል። የሆነ ሆኖ ካነበብኳቸውና ከተረዳኋቸው እውነታዎች በመነሳት፣ የኢኦተቤክ ይህንን አቋም ትደግፈው እንደሆነ እንጃ አትቃወመውም።

ታዲያ ምሥጢራዊ እምነት ወይም ተግባር እና ልምምድ ስንል ምን ማለታችን ነው። ምሥጢራዊ (mystic or mysticism) የሚለው ቃል ከግሪክ የተወረሰ ሲሆን ትርጉሙም የተሰወረ፣ የተደበቀ ምሥጢራዊ ማለት ነው። ሜሪያም ዌብስተር መዝገበ ቃላት " ከአንድ እውነታ ወይም ከመለኮት ጋር በምሥጢራዊ ወይም በተሰወረ መልኩ መዋሃድ፣ መተሳሰር ወይም በቀጥታ ግንኙነት መፍጠር። እንደዚሁም ሊጨበጥ፣ በስጋዊ ህዋሳት ሊደረስበት በማይችል መንገድ ከአምላክ ጋር፣ ከመንፈሳዊ እውነት ወይም ከእውነታ ጋር መዋሃድ፣ መተሳሰር፣ መቆራኘትን ያጠቃልላል" በማለት ይተረጉመዋል። በጊዜና በቦታ እጥረት ምክንያት ብዙ ማብራሪያ በዚህ ሥፍራ መስጠት ባይቻልም፣ ቀደም ሲል የተጠቀሰው የ online ትምህርት የሚያስተምረው ምሥጢራዊ በሆነ መንገድና ዘይቤ ከእግዚአብሔር አምላክ ጋር እንዴት መገናኘት፣ መቆራኘት፣ መተሳሰር እንደሚቻል የሚያስተምር ትምህርት ነው ማለት ነው። ይህ ምሥጢራዊ ዘይቤ ወይም መንገድ እንደ ኢኦተቤክ አስተምህሮ መሠረት ማንም ሰው ሊያውቀው ወይም ሊደርስበት የሚችል የእውቀት ጥበብ እንዳልሆነ ይነገራል።

እንግዲህ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት፣ መቆራኘት፣ መተሳሰር በራሱ ኢክርስቲያናዊ / የስህተት ትምህርት አይደለም። በርካታ ምሳሌዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ በማቅረብ ሃሳቡን መደገፍ ይቻላል። ችግሩ ወይም ስህተቱ የሚገኘው ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት፣ ለመቆራኘት፤ እግዚአብሔርን ለማወቅ የተለየ ማንም እንደዚሁ ሊረዳው ወይም ሊያውቀው በማይችል ምሥጢራዊ mystical በሆነ መንገድ ብቻ ነው የሚቻለው የሚለው አቋም ላይ ነው። ይህንን ዓይነት አቋም እና ትምህርት ሲያስተምሩና ሲያራምድ የነበሩ ከሁለተኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ የነበሩ 'የጥንት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች' "Early Church Fathers" በመባል የሚታወቁ እንደነበሩ ይታወቃል። ነገር ግን ይህንን የሚመስል ትምህርትም ሆነ አቋም፣ በየትኛውንም በቀኖና በተወሰኑት ቅዱሳን መጻሕፍት ውስጥ (66ም ሆነ 81) አናገኝም። ይልቁንም የምናገኘው ከእግዚአብሔር በቀጥታ መገናኘት ይቻላል፣ ይኸውም በክርስቶስ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው የሚል ሃሳብ ነው። አለቀ። ዮሐንስ በጻፈው የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ውስጥ፤ [ዮሐንስም የጻፈበት ዘመን እንደዚህ ዓይነት የግኖስቲክስ እና በአህዛብ ፍልስፍና ላይ የተመሠረተ የስህተት ትምህርት በረቀቀ ሁኔታ በክርስቲያኖች ዘንድ ሰርጎ ገብቶ በነበረበት ጊዜ በመሆኑ እና ይህንኑ የስህተት ትምህርት ለመቃወም አቅዶ የጻፈው እንደመሆኑ] - በመጀመሪያው ምዕራፍ ቁጥር 18 ላይ "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።" በማለት እግዚአብሔርን ልናውቀው፣ ልንረዳው፣ ልንቀርበውና ከእርሱ ጋር ህብረት ልናደርግ የምንችለው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ እንደሆነ ያስረግጥናል። ሰው አይደለም፣ ኤጲስቆጶስ አይደለም፣ መልአክ አይደለም እንደገናም ሥርዓት ወይም ልምምድ አይደለም።

ቀደም ሲል የጠቀስውን ማስታወቂያ ካነበብኩኝ በኋላ ብዙ አሰላሰልኩኝ፣ ብዙም አነበብኩኝ። የበለጠ እውቀት መረዳትና መረጃ እንዲኖረኝ በማሰብ ስለ መጀመሪያዎቹ የአብያተ ክርስቲያናት ዓመታት ታሪክ፤ ስለ ቀድሞ አባቶች አቋምና ትምህርት እንደዚሁም የእግዚአብሔርን ቃል (መጽሐፍ ቅዱስን) አገላበጥኩኝ። እናም አሁን ከመቼውም በበለጠ የግኖስቲክ አስተሳሰቦችና ትምህርቶች፣ የአህዛብ ተውፊቶችና ልምምዶች እንደዚሁም የግሪክ ፍልስፍና አቋሞችና ትምህርቶች በሚገባ በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት፣ ሥርዓት እና ትምህርት ውስጥ ሰርገው ለመግባታቸው ምንም ዓይነት ጥርጥር የለኝም።

ለምሳሌ እራስን/ሥጋን የመጉዳት ascetic ልምድ፣ ምነና እና የምንኩስና ሕይወት፣ ስለ መለኮታዊ እውቀት/ስለ እግዚአብሔር እና ስለ ደኅንነት ሊያውቁ እና ሊረዱ የሚችሉ ብቃት የሚኖራቸው የተለዩ / የተመረጡ ሰዎች ብቻ እንደሆኑ የሚሉት በጥቂቱ እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። ቴዎሲስ theosis ማለትም ሰው መለኮት ይሆናል / ሊሆን ይችላል አለዚያም ደኅንነት ሰው ወደ መለኮትነት ሲቀየር ፍጻሜን ያገኛል የሚል ትምህርትም ከምሥጢራዊ የትምህርት ዘርፍ mysticism የመነጨ ነው። አንዳንዴ ሳስበው አንድን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የእምነት ተከታይ “መለኮት ለመሆን ተጠርተሃል/ተጠርተሻል ወይ?” ብዬ ብጠይቅ ምን ዓይነት መልስ አገኝ ይሆን ብዬ እመራመራለሁኝ። ከዚህ የበለጠ የስህተት / የመናፍቅንነት ትምህርት ምን አለ? ገና ሲጀመር የሰው ልጅ ከነበረው ክብሩና ከተመደለበት ሥፍራ ለመባረር የበቃው - በሰይጣን ተገፋፍቶ - እንደ እግዚአብሔር / መለኮት ለመሆን በመሞከሩ አይደለም እንዴ? ዛሬ በአሸበረቀ እና በሚማርክ ቃላቶችና የቃላት ዝርዝር (ተርሚኖሎጂዎች) ተውቦ መቅረቡ የተለየ ሊያደርገው አይገባም። ሰይጣን ከእኔ ራቅ!

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የበግ ልምድ የለበሱ ነጣቂ ተኩላዎች እንደሚመጡ ባያስጠነቅቀን ኖሮ (ማቴ 7፡-15)፣ ወይም ሐዋርያው ጳውሎስ “እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፥ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል” ከሚያስቱ አስተማሪዎች እንድንጠነቀቅ ባያመክረን ኖሮ ምን እንሆን ነበር? ማስጠንቀቂያው በግልጽ ተሰጥቷል። እኔ ማስታወሴ ነው።

የእግዚአብሔር በረከት ይብዛላችሁ!